# የገንዘብ ሚኒስቴር

## በገዢው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ

## አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2012

ገንዘብ ሚኒስቴር

ህዳር 2012 ዓ.ም

# በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2012

1. <u>አውጪው ባለሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 64 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

2. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

1/ "ታክስ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው።

2/ "አዋጅ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 (እንደተሻሻለ ) ነው።

3/ "በገዥው ተይዞ የሚከፈል ታክስ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ (7) በተደነገገው መሰረት በሀገር ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት የዕቃና አገልግሎት ግብይት ሲከናወን ተከፋይ ከሆነው ታክስ ላይ ተቀንሶ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ የሚደረገው 50% የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው።

4/ "ወኪል" ማለት ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ላይ በገዥው ተይዞ የሚከፈልን ታክስ ቀንሶ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ የሚያደርግ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የግል ድርጅት ነው።

5/ "ታክስ ከፋይ" ማለት ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበና ለወኪሎች ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚያቀርብ ሰው ነው።

6/ "ደረሰኝ" ማለት ታክሱን ቀንሰው የሚያስቀሩ ወኪሎች በታክስ ባለስልጣኑ እውቅና የሚያሳትሙት ወይም በተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ስርአት (IFMIS) ተጠቅመው በማተም ታክሱ ተቀንሶ ለመቅረቱ ማረጋገጫ እንዲሆን የሚሰጡት፣ የተያዘውን የታክስ መጠን የሚያሳይ ሰነድ ነው።

7/ "ባለስልጣን" ማለት እንደአግባብነቱ የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የክልል መንግስት እንዲሁም የከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣናት ናቸው።

8/ "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው።

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ታክሱን ቀንሰው እንዲያስቀሩ በመመሪያ ቁጥር 27/2002 በተወከሉ እንዲሁም በተከታታይ በሚወጡ መመሪያዎች የሚወከሉ የፌዴራል፣ የክልል መንግስታትና የከተማ አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች እንዲሁም የተመረጡ የግል ድርጅቶች በሚያከናውኑት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 5. ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ላይ ተቀናሽ ተደርጎ ስለሚያዝ ታክስ

1/ ማንኛውም ወኪል ለአቅራቢው መክፈል ካለበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ውስጥ 50% (ሀምሳ በመቶ) ብቻ ቀንሶ በማስቀረት ቀንሶ ያስቀረውን ታክስ በየወሩ የሚቀጥለው ወር በገባ በ30 ቀናት ውስጥ በታክስ ከፋይነት ለተመዘገበበት የታክስ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለአቅራቢው ከሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ውስጥ 50% ወኪሉ ቀንሶ ካስቀረ በኋላ ቀሪውን 50% (ሀምሳ በመቶ) ከእቃ ወይም ከአገልግሎት ክፍያው ጋር ለአቅራቢው ወዲያውኑ መክፈል አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ተቀንሶ የሚቀረው ታክስ በቅድሚያ ክፍያ እና በከፊል በሚፈፀሙ የአገልግሎት ወይም የዕቃ አቅርቦት ክፍያዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4/ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ክፍያ የሚፈፀመው በውጭ ሀገር ገንዘብ ከሆነ በባንክ በኩል ወደ ብር በተቀየረበት ገንዘብ መጠን ላይ ታክሱ የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

5/ ሜጋ ፕሮጀክቶችን የሚያከናውኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለግንባታ ሥራ ከሚፈፅሙት ክፍያ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰላው የአገልግሎቱ ዋጋ ነው ተብሎ በሚወሰደው 50% ላይ ብቻ በመሆኑ፣ ይህንኑ ታክስ ቀንሰው ማስቀረት አለባቸው፡፡

6/ የኢትዮጵያ መንግሥት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከውጭ አገር በብድር ባገኙት ገንዘብ ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ክፍያ የሚፈፀመው በቀጥታ በአበዳሪው ከሆነ ከተከፋዩ ሂሳብ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም፡፡ ስለሆነም ሥራ ተቋራጩ የተጨማሪ እሴት ታክሱን ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ያደረገ መሆኑን መከታተል እንዲቻል አሠሪ መ/ቤቶች መረጃውን ክፍያ በተፈፀመ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣኑ ማስታወቅ አለባቸው፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ላይ የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስ በገኘሩው አይያዝም፡፡

የገንዘብ ... ሚኒስቴር
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation N° 2

## 6. ታክሱ ተቀናሽ የሚደረግበት ግብይት ዋጋ

1/ ወኪሉ ከብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) ብር በላይ ዋጋ ያለው የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ መፈፀም የሚችለው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ላይ ብቻ ነው፡፡

2/ ለታክስ ከፋዩ በአንድ ጊዜ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ 20,000 (ሀያ ሺህ) ብር በላይ ሲሆን ወኪሉ የታክሱን 50% (ሀምሳ በመቶ) ቀንሶ ማስቀረት ይኖርበታል፡፡

3/ ለታክስ ከፋዩ በአንድ ጊዜ የሚከፈለው ክፍያ ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) እና ከዚያ በታች ከሆነ ወኪሉ የታክሱን ሂሳብ ጭምር ለታክስ ከፋዩ መክፈል ይኖርበታል፡፡ ታክስ ከፋዩ በዚህ አይነት የሰበሰበውን ታክስ ለታክስ ባለስልጣኑ አስታውቆ የሚከፍለው በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው ወይም ድርጅት የሚሰጥ አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ 23 በገዥው ስለሚሰበሰብ ታክስ በተደነገገው መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 7. የወኪል ግዴታ

ማንኛውም ወኪል፡-

1/ ታክሱን ቀንሶ ለማስቀረት በታክስ ባለስልጣኑ ተመዝግቦ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ሰርተፊኬት የመውሰድ ፤

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (3) ከተጠቀሰው በስተቀር በሚፈፅመው በእያንዳንዱ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ላይ 50% ቀንሶ የመያዝ፣

3/ ከእያንዳንዱ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ቀንሶ በሚይዘው ታክስ መጠን ልክ ለዕቃ ወይም ለአገልግሎቱ አቅራቢ ወዲያውኑ በገዥው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የመስጠት፣

4/ ለእያንዳንዱ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከዕቃ ወይም ከአገልግሎት አቅራቢው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የመቀበል፣

5/ በወሩ ውስጥ ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ቀንሶ የያዘውን ታክስ በሙሉ ወሩ በተጠናቀቀ ባለው ቀጣይ ወር የ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ የማድረግ፣

6/ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ጋር በተያያዘ ክፍያ የተፈፀመለትን ሰው ወይም ድርጅት ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፣ የተፈፀመውን ግብይት ዋጋ እና ተቀንሶ የቀረውን የታክስ መጠን የሚያሳይ ዝርዝር የታክስ ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ ሞልቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ ከሚያደርገው ሂሳብ ጋር የማቅረብ፣

7/ በዚህ መመሪያ መሰረት በወሩ ውስጥ የተከናወነ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት በሌለበት ወይም አንቀጽ 5 ንዑስ በአንቀጽ (3) መሰረት በግብይቱ ላይ የሚከፈለውን ታክስ ለአቅራቢው የተከፈለ በመሆኑ ተቀንሶ የተያዘ ታክስ አለመኖሩን ወሩ በተጠናቀቀ ቀጣይ 30 ቀናት ውስጥ ለተመዘገበበት የታክስ ባለስልጣን በደብዳቤ ማረጋገጫ የማቅረብ፣

ግዴታ አለበት፡፡

## 8. ታክስ ስለማቀናነስ እና የተመላሽ ጥያቄ

1/ ታክስ ተቀናሽ የተደረገበት ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢ ከወኪሉ በተሰጠው ታክሱ ተቀናሽ መደረጉን በሚያረጋግጠው ደረሰኝ ላይ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን በግብአት ላይ ለከፈለው ታክስ ማካካሻ ሊያውል ይችላል፡፡

2/ ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢው የታክስ ሂሳብ ተቀናሽ ተደርጎ የተሰጠውን ዋናውን ደረሰኝ ታክሱን በሚያስታውቅበት ጊዜ ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

3/ ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት ጊዜ በተቀበለው ደረሰኝ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ለሁለት ወራት በግብይት ላይ ከተከፈለ ታክስ ወይም ተከፋይ ከሚሆነው ታክስ ጋር እንዲካካስ አድርጎ በደረሰኙ ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን በግብአት ላይ ከተከፈለው ወይም ተከፋይ ከሚሆነው ታክስ የበለጠ ሆኖ ከተገኘ የተመላሽ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የቀረበውን ጥያቄና የታክስ ሂሳብ መርምሮ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ45 (አርባ አምስት) ቀናት ውስጥ ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ሂሳብ መመለስ አለበት፡፡

5/ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ከ50% በላይ የሚሆነውን ግብይት የሚያከናውነው ከወኪሎች ጋር ከሆነ በደረሰኙ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በግብአት ላይ ከተከፈለ ታክስ ወይም ተከፋይ ከሚሆነው ታክስ ጋር እንዲካካስ አድርጎ በብልጫ የሚታየው ገንዘብ እንዲመለስለት ለባለሥልጣኑ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፤ ባለስልጣኑም ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ሂሳብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መመለስ አለበት፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

## 9. ተቀናሽ የተደረገውን ታክስ ገቢ ስለማድረግና ስለማከፋፈል

1/ ታክስ ቀንሶ የመያዝ ግዴታ የተጣለበት ወኪል ቀንሶ የያዘውን ታክስ ገቢ የሚያደርገው ለታክስ ከፋይነት ለተመዘገበበት ለታክስ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

2/ የክልል መንግስታትና የከተማ አስተዳደር ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የገቢዎች ሚኒስቴር ቅ/ጽ/ቤቶች በዚህ መመሪያ መሰረት ተቀናሽ ተደርጎ ገቢ የተደረገላቸውን ታክስ ተቀናሽ የተደረገበት ታክስ ከፋይ ለተመዘገበበት የታክስ ባለስልጣን መላክ አለባቸው፡፡

3/ የክልል መንግስታትና የከተማ አስተዳደር ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የገቢዎች ሚኒስቴር ቅ/ጽ/ቤቶች ገቢ የተደረገላቸውን ታክስ ለሚመለከተው የታክስ ባለስልጣን ሲያከፋፍሉ በገቢዎች ሚኒስቴር ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ለሚቀርበው ግብር አፈፃፀም ከተዘጋጀው ቅጽ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ቅጽ በመጠቀም ገንዘብ ለተላከለት የታክስ ባለስልጣን ዝርዝር ሪፖርቱን ጭምር መላክ አለባቸው፡፡

## 10. ተቀናሽ ተደርጎ ለሚያዝ ታክስ የሚሰጥ ደረሰኝ

1/ የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የክልል እና የከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣን ተቀናሽ ተደርጎ ለሚያዝ ታክስ የሚውል ደረሰኝ እንዲያሳትም ለወኪሉ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2/ ወኪሉ ከታክስ ባለስልጣን በሚሰጠው ፈቃድ ደረሰኝ ያሳትማል፣ ባለስልጣኑ የሚያወጣውን የደረሰኝ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት ተከትሎ ደረሰኙን ጥቅም ላይ ያውላል፡፡

3/ ወኪሉ ተጨማሪ ደረሰኝ እንዲያሳትም የሚፈቀድለት ቀደም ሲል ባሳተመው ደረሰኝ ቀንሶ የያዘውን ታክስ በትክክል ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረጉ እየተረጋገጠ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተደነገገው ቢኖርም በተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ስርአት (IFMIS) ተጠቅመው ደረሰኝ በማተም ታክሱ ተቀንሶ ለመቅረቱ በመንግስት ባለበጀት መ/ቤት የሚሰጠውን በገኘው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለመስጠት የታክስ ባለስልጣኑ ፈቃድ አያስፈልገውም፡፡

## 11. በገኘው ተይዞ የተከፈለውን ታክስ ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

ባለስልጣኑ፡-

1/ ወኪሉ ያሳተማቸውን ደረሰኞች በመመርመር የታክሱን አሰባሰብ ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር
የገቢዎች ሚኒስቴር
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

2/ ወኪሉ በፈፀማቸው ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት ታክሱን በትክክል ቀንሶ ያለማስቀረቱን ወይም የቀነሰውን ታክስ ለባለስልጣኑ ገቢ ያለማድረጉን ሲያረጋግጥ ወኪሉ በልዩነት የሚፈለገውን ታክስ፣ ወለድ እና መቀጫ ጨምሮ እንዲከፍል ያደረጋል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀው ቢኖርም ወኪሉ የዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢው ደረሰኝ በሰጠበት ወር በገባው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ካልሰጠ መስጠት ከነበረበት እና እስከሰጠበት ጊዜ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ወለድና የዘገየበት ቅጣት እንዲከፍል ያደርጋል።

## 12. የሂሳብ አመዘጋገብ

1/ ተቀናሽ ሆኖ የሚቀረው ሂሳብ በተከፋይ የሒሳብ መደብ ቁጥር 5059 ይመዘገባል።

2/ የመንግስት ባለበጀት መ/ቤት በተከፋይ የተያዘውን ገንዘብ ለባለስልጣኑ ገቢ ሲያደርግ የተከፋይ ሂሳብ ወጪ በሚል ይመዘገባል፣ ይህንኑም ለሚኒስቴሩ ወይም ለክልል እና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ በየወሩ በሚያቀርበው የሒሳብ ሪፖርት ውስጥ ያካትታል።

## 13. አስተዳደራዊ መቀጫና የወንጀል ቅጣት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ያልተወጣ ወኪል በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 37 መሰረት ወለድ እና በአንቀጽ 106 መሰረት አስተዳደራዊ መቀጫ እንዲሁም የወንጀል ቅጣቶች ተፈፃሚ ይደረጉበታል።

## 14. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ ከህዳር 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር 15 ቀን 2012 ዓ.ም.

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2